# የእኛ “ወጋጎዳ”

ከወሰንሰገድ ገ/ኪዳን (ጋዜጠኛ)



-1-

በማንኛችንም ህይወት ውስጥ ሰዎች አሉ፡፡በእድሜ ዘመናችን፣ በአጋጣሚ፣ እንደው በድንገት፣ እንደው እንደዋዛ ወደህይወታችን ውስጥ ገብተው የሚቀሩ ሰዎች አሉ፡፡ አንድም፣ ሁለትም፣ ሶስትም፣ ከዚያም በላይ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ብቻ በማንኛችንም ህይወት ብዙ ሰዎች አሉ፡ በእኛ ውስጥ ህይወት ዘርተው፣ በ”ታሪካችን” ውስጥ በቅለው፣ ሰፍተው ተንሰራፍተው እንደዋርካ ገዝፈው የሚኖሩ፣ በልዩ ሁኔታ የሚታወሱ ወይም የምናስታውሳቸው ሰዎች አሉ፡- ተፅዕኖ ፈጣሪዎች፡፡

ከነዚህ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች መሃል ደግሞ ተለይተው የሚገኑ፣ ብቻቸውን ብዙ…የብዙ ብዙ የሚሆኑ፣ በሙያቸው፣ በግብራቸው፣ በህይወት ተመክሮአቸው …ወዘተ የሚልቁ፣ በእኛ ዘንድ ብቻ ሳይሆን በብዙዎች ልቦና ውስጥ የራሳቸውን አሻራ አትመው የሚኖረ ጥቂት ሰዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ መሰል ሰዎች መሀል አንዱ ነው ዛሬ ብዕሬን ከአፎቱ እንድመዝ ግድ ያለኝ፡፡ ያ ሰው ማነው? በአንዲት ቃል፣ በትውልድ ቀዬው ቋንቋ በደምሳሳው ልግለፀው፡፡ ያ ሰው “ወጋጎዳ” ነው፡፡ የ“ወጋጎዳ”ን ትርጉም ወደ ኋላ ላይ እመለስበታለሁ፡፡

ወዳጄ እንዳለጌታ ከበደ በታህሳስ ወር 2005 ዓም መገባደጃ ለንባብ በበቃው “አዲስ ታይምስ” መፅሔት ቁጥር ቅፅ 1 ቁጥር 12 ዕትም “የማይመጣን ነገር መጠበቅ” በሚል ርዕስ ያስነበበን ፅሁፍ ነው አንዳች የንሻጤ ስሜት የፈጠረብኝ፡፡ በሌላ አገላለፅ እኔም የበኩሌን እተነፍስ ዘንድ የመነቃቃት ስሜት የፈጠረብኝ የደራሲ እንዳለጌታ ከበደ ደግነት ነው፡፡ ደ..ግ…ነት!!

እንዳለጌታ ከበደ ዘመናችንን የተጣባውን የንፉግነት ድልድይ ተሻግሮ በሕይወታችን ውስጥ ያለፉትን፣ በልቦናችን ጡብ ያስቀመጡትን፣ ለእኛነታችን እኛነት አንዳች ድርሻ ያበረከቱትን ሰዎች እናመሰግን ዘንድ፣ እናከብራቸው ዘንድ፣ እንፈልጋቸው ዘንድ ነው የወተወተን፡፡ ከዚህ የበለጠ ደግነት ምን አለ!? እናም በደግነት መንፈስ - “ከደጋጎቹ” መሐል አንዱን ዘከራቸው፡- አቶ አሠፋ ጫቦን፡፡ አስታዋሽ አይጥፋ!!

ለማንኛውም ደራሲ እንዳለጌታ ከበደ ለዚያ ደግ መጣጥፉ መነሻ ያደረገውን ጉዳይ ልዋስ፡- “….መምህራን በተለያዩ አጋጣሚዎች በህይወታችን ውስጥ ያልፋሉ፡፡ በህሊናችን ውስጥ አስቀምጠው ሳለፉት ጡብ ግን በዝንጋጌ ወይም በክፋት ብዛት የምስጋና ቃል አንቸራቸውም፡፡ አበርክቶአቸውን ሳናሳውቅላቸው እና ሳናውቃቸው እንደዘበት ያልዳፋሉ፡፡ ያርፋሉ፡፡ ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ጋሽ አሠፋ ነው፡፡ አሠፋ ጫቦ፡፡ የጨንቻው፡፡ ይህ ሰው በውስጤ ብዙ ነገር ዘርቷል፡፡…ይህ መጣጥፍ  የምስጋና ቃል እንደሆነ እንዲታወቅልኝ እሻለሁ፡፡ ይህ መጣጥፍ አሠፋ ጫቦ ሆይ የት ነው ያለኸው? ለማለት የቀረበ የናፍቆት ደብዳቤ እንደሆነ እንዲታወቅልኝ እሻለሁ…” ይላል እንዳለጌታ ወደ ዋናው ጉዳይ ሲንደረደር፡፡ ይቀጥላል፡፡ አሠፋ ጫቦን ይተርከዋል፡- ከታሪኩ እየጨለፈ፡፡ የአቶ አሠፋ ጫቦ ታሪክ ግን ተጨልፎ የሚያልቅ አይደለም፡፡ ሰውየው ብዙ ነዋ!! የብዙም ብዙ ነው፡፡

ጋዜጠኛው አሠፋ ጫቦ፣ የሕግ ባለሙያው አሠፋ ጫቦ፣ የሠብአዊ መብት ተሟጋቹ አሠፋ ጫቦ፣ አንደበተ-ርትዑ አሠፋ ጫቦ፣ እስረኛው አሠፋ ጫቦ፣ ፖለቲከኛው አሠፋ ጫቦ፣ ፀሐፊው (ደራሲው) አሠፋ ጫቦ፣ የጨንቻው አሠፋ ጫቦ…ወዘተ፡፡ ብዙ ነው፡፡ ለዚህ ነው  አሠፋ ጫቦን “ወጋጎዳ” ነው ያልኩት፡፡ ወጋጎዳ  ማለት በጋሞኛ እና በአካባቢው ተቀራራቢ ቋንቋ “ታላቁ ጌታ” ማለት ነው፡፡ በልማዳዊ አባባል ሐብታም ነው ለማለት ሲፈለግ “ጌታ ነው” እንደሚባል አፅኦት ስጡልኝ፡፡ አሠፋ ጫቦም “ጌታ” ነው፡- የብዙ ነገር ባለሃብት፡፡

- 3 —

የአሠፋ ጫቦም “ወጋጎዳ”ነት ወይም ባለብዙ ሃብትታምነት የሚጠቀለለው ወይም የተጠቀለለው እና ለእኛ ትውልድ የተገለጠው በላቀ የፀሐፊነት (የደራሲነት) ክህሎቱ ነው፡፡ አሠፋ ጫቦ ሲፅፍ

ለሁሉም ሰው በሁሉም ልክ እየሰፋ ነው፡፡ ከሊቅ እስከ ደቂቅ፣ እኔ ነኝ ካለ ምሁር እስከ ተራው ሰው (ተራ ሰው የሚባል ካለ)፣ ከአለቃ እስከ ምንዝር...ወዘተ ለሁሉም የሚመጥን፣ ለሁሉም በሚመጥን፣ ለሁሉም በሚስማማ መልኩ ሃሳቡን ፈትፍቶ ማጉረስ የሚችል ድንቅ ፀሐፊ ነው፡፡

አሠፋ ጫቦ የመጠቀውን የፖለቲካ አስተሳሰብ፣ የመጠቀውን የፍልስፍና ፅንሰ ሃሳብ፣ የመጠቀውን የሕግ አተያይ ወዘተ አለዝቦ፣ አዋዝቶ፣ ደቁሶ፣ ሰልቆ፣ ለማንኛውም ሰው በሚገባ ሁኔታ ማቅረብ የሚችል ፀሐፊ ነው፡፡ አሠፋ ጫቦ ከፍ ዕውቀቱን ከፍ አድርጎ ለማሳየት ሲል አይራቀቅም፡፡ ለመራቅ አይከጅልም፡፡ አሠፋ ጫቦ፣ ልክ እንደተረት አባት ነው፡፡ ፅሁፉ፣ ሰውየው ራሱ አጠገባችን ቁጭ ብሎ የሚተርክልን፣ የሚያወራን፣በጆሮአችን የምንሰማው ያህል የመግዛት ኃይል አለው፡፡ ለልብም፣ ለዓይንም፣ ለህሊናም መቅረብ የሚችል ፀሐፊ ነው፡- አሠፋ ጫቦ፡፡

እንዳለጌታ ከበደ እንዳለው ቋንቋው ውብ ነው፡፡ ቀላል ነው፡፡ ትልቁን፣ እጅግ ትልቁን ሃሳብ ወይም ጉዳይ ገምድሎ፣ ከርትፎ፣ አድቅቆ፣ ልም አድርጎ ማቅረብ ይችልበታል፡፡ እኛ ቦታ የማንሰጠውን ወይም ያልሰጠነውን ጉዳይ አሳድጎ፣ ከፍ አድርጎ፣ አግዝፎ መከሰት ይሆንለታል፡፡ እሱ በፈቀደው መንገድ ህሊናን ተቆጣጥሮ እስከጉዳዩ መጨረሻ ድረስ ይዞ መንጎድን የተዛነ ፀሐፊ ነው፡፡

አሠፋ ጫቦ ሲፅፍ ልክ እንደሠዓሊ ነው፡፡ በብዕር ቀለም፣ በቃላት ሐረግ፣ በዓረፍተነገራት ሕብረት የሚታይ፣ የሚጨበጥ፣ የሚዳሰስ ምስል በዓይነ ህሊናችንና በዓይነ ልቦናችን ውስጥ መቅረፅና ማሳየት የሚችል ፀሐፊ ነው፡፡ ይህንን ዓይነቱን ሥዕል ለማሳየት ብሎ ሲፅፍ አይጨነቅም፡፡ እጥር፣ ቅልብጭ ባለ ትረካ፣ አስከፊውንና አስጨናቂውን ሁኔታ ወይም ነገር ዘና ብሎ አንባቢን እያዝናና መተረክ ይችልበታል፡፡ እነሆ አብነት በአንድ ወቅት "የሞተ ተጎዳ" በሚል ርዕስ ከፃፈው ፅሁፍ እንዋስ፡፡

አሠፋ ጫቦ ጥር 16 ቀን 1971 ዓም "የኢትዮጵያ አብዮት ከየት - ወዴት? ትናንት - ዛሬ - ነገ" የሚል ሰፋ ያለ ፅሁፍ ለደርግ አባላቶች በትኖ ነበር፡፡ ያ ፅሁፍ በደርግ ጥርስ ውርስ እንዳስገባው ነው እሱ የሚተርከው፡፡ ምክንያቱም ከዚያች በኋላ እጅግ በጣም የሚቀርባቸው የደርግ አባላት ሳይቀሩ ፊት ነስተውት ነበር፡፡ ሆኖም ወደቤተመንግስት ጎራ ማለት አልተወም፡፡ የካቲት 21 ቀን 1971ም ቤተመንግስት ጎራ ውሎ ነው የተመለሰው፡፡ ሠላም አሳድረኝ ብሎ፡፡ ቤቱ ውስጥ ከራሱ ፓርቲ አመራር አበላት ጋር ተወያይቶ ሊሸኛቸው ወጣ፡፡ በዚያ ምሽት

እንደወጣ አልተመለሰም። ሲጠብቀው የነበረው ሁኔታ ባልጠበቀው ሁኔታ ገጠመው። የገጠመውን በራሱ ብዕር ከተረከው ቃል በቃል ብንቀነጭብ ነው የሚሻለው። እነሆ፡-

"…መውጣት ሲጀምሩ ሲጋራ ፍለጋ ኪሴ ውስጥ ብገባ አልቆ ኖሯል። ብርድ ቢጤ ጀምሯል። ከላይ የለበስኩት ስስ T-shirt ነው። ፎቅ ወጥቼ ከምወርድ አንደኛውን ገዝቼ ለመግባት ከግቢው ወጣሁ። የሠፈራችን ኪዎስክ ያለው ከእኛ ቤት ማዶ (Diagonal) ነው። ቤታችን ያለው አራት መንገድ መገናኛ ላይ ነው። ከላይ አራት ኪሎ፣ ከምኒሊክ ወርዶ ራጉኤል የሚባለው መንገድ አለ። ምዕራብ ምስራቁ መንገድ ከካዛንቺስ በእንደራሴ መንገድ አድርጎ አቧሬ የሚወጣው ነው። ራስ ሙሉጌታ መንገድ ወደሚባለው መንገድ የሚሻገረው ነው። አራት ማዕዘኑ ከላይኛው ከንፈር ጥግ የቀድሞው አስፋወሰን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ፊት ለፊትም ሱቅ አለች። አልፎ አልፎ ሲጋራ ከዛ እገዛለሁ። ሁሌ የማገኛቸው አንድ ምራቃቸውን የዋጡ የሚመስሉ አጠር ያሉ ሴት ናቸው። አንድ ፓኮ ዊኒስተን ሲጋራ ሰጡኝ። አንደ ለማቀጣጠል ፈልጌ ክብሪት ብጠይቅ ‹በከሰሉ እሳት ለኩስ› አሉኝ። ሲጋራ በከሰል ሆነ ሌላ እሳት ወይም ከሌላ ሲጋራ መለኮስ አልወድም። ‹እርካታውን› የሚቀንሰው ይመስለኛል። ሆኖም እያጉተመተምኩ አያይዤ አንድ ስቤ፣ መንገዴን ለመቀጠል ፊቴን አዞርኩኝ።…."

አሠፋ ጫቦ "የምሽት መብረቅ" የሚል ንዑስ ርዕስ ሰጥቶ ትረካውን ይቀጥላል። እንዲህ፡-

"….ለጦር ሜዳ እንዲሆን ብለው ወታደሩን በ‹አስደንጋጭ ድምፅ› ያሰለጥኑታል መሰለኝ። አስደንጋጭ፤ አደንዛዥ፣ አስፈሪ፣ የሚያርድ ድምፅ ማግኘት የሙያው ዘርፍ ሣይሆን አይቀርም። ያየህ ይራድ እንዲሉ ‹የሰማህ ይራድ› ለማለት።… ወጣ እንዳልኩ ግድግዳውንም አስፋልቱንም ሊሰነጣጥቅ የሚችል ድምፅ ሰማሁ። ከፍተኛ ቂጣ ያለው ይሁን እንጂ ከየት ወዴት፣ ማን ላይ እንዳተኮረ መገመት አልቻልኩም። ብቻ በሚያስፈራ የጩኸት ውቅያኖስ ውስጥ ተዋጥኩ። ሁለቱም እግሬ በሾኬ የተመታሁ መሰለኝ። መመታቴ ሳይሰማኝ በሙሉ ቁመናዬ ፊት ለፊት አስፋልቱ ላይ ተዘረርኩ። እንደ ግንድ ዥው ብዬ መውደቄን አስታውሳለሁ። ለመጮህ ይሁን ለመጠየቅ ከአፌ ጩኸት ነገር የወጣ ይመስለኛል። ያንን ያሰኘኝ አንድ ግዙፍ እጅ አፌን አፈነው። ከትልቅነቱ የተነሳ አፌን ብቻ ሳይሆን ግማሽ ፊቴን የሸፈነው ይመስለኛል። ይኼኛው የዚህኛው የሥራ ምድብ መሆን አለበት። ከወድኩበት አራት ይሁኑ 24 አንጠልጥለውና ጎትተው መኪና ውስጥ ሲያስገቡኝ ይታወቀኛል። ተለቅ ያለ መኪና ቢያመጡ ጥሩ ነበር። በእነሱ ብዛት፣በመኪናዋ በር ማነስ የተነሳ ጭድ ጆንያ ውስጥ እንደሚከት አድርገው ከተቱኝ።…."

(ከኢትኦጵ መፅሔት ቅፅ 2 ቁጥር 21 የካቲት 1993 ዓም ዕትም የተወሰደ)

አሠፋ እንዲህ ያለ ፀሐፊ ነው፡፡ መራሩን ነገር እያለዘበ እያጣፈጠ ይፅፈዋል፡፡ከሰፋ በእያንዳንዱ አንዳንዱ አንቀፅ ውስጥ ሲተርክልን በሚቀጥለው አንቀፅ ውስጥ የሚያስከትለውን አስቀድሞ ይነግረናል፡፡ ይኼንን ነገር የቲያትር ባለሙያዎች ንግር ይሉታል፡፡ ለምሳሌ ብርጭቆ ሲሰበር ቀጥሎ ግጭት አለ እንደማለት፡፡ የአሰፋ ሲጋራ በክሰል ማቀጣጠል የሚቀጥለውን አስደንጋጭ ገጠመኝ ጠቋሚ ይመስለኛል- ለእኔ፡፡ ከአፉ በላይ ግማሽ ፊቱን የሸፈነው አፍ የደርግ መንግስት ሠፊ የአፈና መዳፍ ይከስትለኛል፡፡ አሰፋ በቁጥብ አገላለፅ ብዙ እጅግ ብዙ ነገሮችን ማሳየት የሚችል ድንቅ ፀሐፊ ነው፡፡ ያንን ሰው ነው እኔ "ወጋጎዳ" የምለው፡፡

## -4-

አሠፋ ጫቦ ጨንቻ ነው ውልደቱ፡- ደቡብ ክልል፡፡ የተወለደበትን ዓመተምህረት በውል አያውቀውም፡፡ ብቻ ጣሊያን ኢትዮጵያን ለቆ እንደወጣ ወደዚህች ምድር እንደመጣ ያውቃል፡፡ እኔን የሚገርመኝ ጨንቻን ለቆ የወጣበት ሁኔታ ነው፡፡ "አምዖ" ነው ከጨንቻ የወጣው፡፡ መብቴ ለምን ተነካ ብሎ ነው ብለው ይሻላል፡፡ ያኔ ደጃዝማች ወልማሪያም የሚባለው የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ነበረ፡፡

"…በመጀመሪያው ተርም መጨረሻ (ገና) አራተኛ፣ በሁለተኛው ተርም መጨረሻ (ለፋሲካ) አምስተኛ፣ በአመቱ መጨረሻ ስድስተኛ ገባሁ፡፡ በሚቀጥለው ዓመት ለገና አንደኛ ከወጣህ ወደ 7ኛ ክፍል ትዛወራለህ ተባልኩ፡፡ ት/ቤት ሲዘጋ አንደኛ ነህ ተባልኩ፡፡ ሲከፈት ግን አራተኛ ወጣህ ተባልኩ፡፡ ነገሩ በስፖርት 69% አግኝቼ የነበረው ተለውጦ 39% ሆነና ነው፡፡ አንድ ልጅ እናቱ ስላለቀሱ ለእሱ ማርክ ከመጨመር ፈንታ ተቀነሰ፡፡ በዚህ በተፈጠረ ጭቅጭቅ የጠ/ግዛቱ ት/ቤቶች ሥራ አስኪያጅ በነበሩት አቶ ቦጋለ ዋለሉ ላይ ተማሪ በተሰበሰበበት ድንጋይ ወርውሬ ሳትኩ፡፡ ከዚያ እግሬ አውጭኝ ብዬ ከት/ቤት ወጣሁ፡፡ ይህ የሆነው ሰኞ ሆኖ ሐሙስ ከጨንቻ ወጣሁ፡፡…"

***(ለጦቢያ መፅሔት ቅፅ 7 ቁጥር 2 1992 ዕትም ከሰጡት ቃለ ምልልስ የተወሰደ)***

ይገርማል!! ቦጋለ ዋለሉ ማለት በደቡብ ክልል የትምህርትን ዘር የዘሩ፣ ነገር ግን ያልተዘመራላቸው ታላቅ "ሐዋርያ" ናቸው፡፡ ከ1901- 1958 ዓም ነው በሕይወት የኖሩት፡፡ በዚያ ጨለማ ዘመን ትውልድን በትምህርት በማነፅ ነፃ ለማውጣት የደከሙ፣ የባከኑ፣ በፅናት የታገሉ የዕውቀት ፋኖ ናቸው፡፡ በጣሊያን ወረራ ወቅት እሳቸው ት/ቤት ሲቀልሱ፣ ወራሪው ሲያቃጥልባቸው፣ ሌላ ቦታ የትምህርት ዳስ ሲድሱ ጣሊያን ሲያፈርስባቸው፣ ካለመታከት የታገሉ "የጀግኖች ጀግና" ናቸው፡፡ በአፄው ዘመንም ሆነ ከዚያ በኂላ ከደቡብ ክልል የወጡ

ምሁራኖች እሳቸው በቆረቆሯቸው ት/ቤት ተምረው ነው። ግን ምን ያደርጋል እኛ "ጀግና" ብለን የምናወድሰው ጠመንጃ ያገቱን ሆነና ሥማቸውንና እንኳ በወጉ ሰምተን አናውቅም። ምስላቸውን እንኳ ለማየት አልታደልንም። እንጂ ቦጋለ ዋለሉ በትውልድ ሊወደሱ፣ ሊታወሱ፣ ሊዘከሩ የሚገባቸው ሰው ነበሩ። ከአሰፋ ጫቦ በላይ የሃገር ዋርካ መሆናቸው ሊነገርቸው የሚገባ "ወጋጎዳ" ናቸው።

እኔ የእኚህን ሰው ታሪክ በመጠኑ ያወቅኩት በጆን ክርስቶፈር ሩፊን ተደርሶ ሁለት የባህር ማዶ ሽልማቶች የተቀዳጀውን ድንቅና የዳጎሰ ረጅም ልብወለድ "አበሻው" በሚል ርዕስ ተርጉመው ያቀረቡት አቶ አያሌው ምትኩ ብሩ፣ ታሪካቸውን ዕፈው ወደማተሚያ ቤት ሲልኩ የማየት ዕድል ስለ ገጠመኝ ነው። የቦጋለ ዋለለ ታሪክ ለተደራሲያን ይቅረብ አይቅረብ ግን እርግጠኛ አይደለሁም። ድምፃዊ ጥበበ ወርቅዬ "ሊጋባ" በሚለው ዘፈኑ ክሊፕ ውስጥ የቦጋለ ዋለሉ ምስል እንደዘበት ሽው ብሎ ሲያልፍ እንደሚያልፍ ያወቅኩትም በዚህ አጋጣሚ ነው።

የሆኖ ሆኖ አሠፋ ጫቦ በእኚህ የትምህርት አርበኛ ላይ ነው ድንጋይ ወርውሮ ጨንቻን ለቆ የወጣው። በዚህ ሁኔታ ከጨንቻ ወጥቶ ነው በብዙ ሰዎች ልቦና ውስጥ፣ በብዙ መልኩ ሰፍቶ ተንሰራፍቶ ለመኖር የበቃው። ከጨንቻ ወጥቶ ነው "ሀገር ሙሉ" የሆነው። "ወጋጎዳ" የሆነው።

# 5

ሌላው የገረመኝ፣ ደራሲ እንዳለጌታን ያስገረመው ነው። ደርግ አስሮታል። ከዕድሜው ከ10 ዓመት በላይ በልቶበታል። ነገር ግን በደርግ ላይ በመረረ ጥላቻ ጣቱን ለመቀሰር አይሞክርም። "....ደርግ 11 ዓመት ያሰረኝ በጥፋቴ ነው። መታሰሬ ሳይሆን መትረፌ ነው የገረመኝ። ‹ጥፋትህ በተለይ› ተብሎ ባይነገረኝም...." ይላል፤ ከላይ የጠቀስነው ጥር 16 ቀን 1971 ዓም ፅፎ ለደርግ ባለስልጣናት የበተነው ወረቀት ወደእስርቤት ለመወርወር ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይጠረጥራል፦ ለጦቢያ መፅሔት በሰጠው ቃል።

"...ጊዜው ረዘመ እንጂ መታሰሩ አስከፍኖኛል ብዬ እገምታለሁ። አገሬን አውቃለሁ የሚለውን ትምክህት አስተነፈሰልኝ። ከመላው ኢትዮጵያ ከሊቅ እስከደቂቅ የመጣበት ስለነበር አገሬን እንደገና በጥሞና ለማየት ዕድል አገኘሁ። የታሰረው አሰፋና የተፈታው አሰፋ ይለያያሉ።.." (ዝኒ ከማሁ)

አሠፋ ጫቦ ተሳስቼያለሁ፣ ተሳስቻለሁ ለማለት አይፈራም። ራስን ማየትን፣ ራስን መመርመርን፣ ነገሮችን ሰፋ እና ጠለቅ አድርጎ ማስተዋልና መፈተሽ እንደሚገባ ደግሞ ደጋግሞ የሰበከ ነው። ይህንን መሰሉን ሃሳቡን ባነበብኩ ቁጥር ትውስ የሚለኝ ጋናዊው

የተመድ ዋና ፀሐፊ የነበሩት ኮፊ አናን በአንድ ወቅት በፈረንጅ አፍ ለሚታተም መፅሔት የሰጡት ቃለ ምልልስ ነው፡፡

ለተመድ ታላቅ ኃላፊነት በቅተዋል፤ እንደው እዚህ ደረጃ ለመድረስ ምክንያት ሆኖኛል፣ ተፅዕኖ አሳድሮብኛል የሚሉት ሰው ወይም ሁኔታ ካለ ሊነግሩኝ ይችላሉ? የሚል ዓይነት ጥያቄ አቀረበችላቸው፡- ጋዜጠኛዋ፡፡ ኮፊ አናን ቅልብጭ ያለ መልስ ሰጡ - አስተማሪዬ የሚል፡፡

ኮፊ አናን የ7ኛ ይሁን የ8ኛ ክፍል ተማሪ ሳሉ አንድ አስተማሪ ወደ ክፍላቸው እንደገባ ያልተጠበቀ ጥያቄ ጠየቃቸው፡፡ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ወደነጩ ቦርድ (White bord) ሄዶ በጥቁር ፓርከር አንድ ሚጢጢ ነጥብ አስቀመጠና "ተማሪዎች ምን ይታያችኋል?" ሲል ጠየቃቸው፡፡ የክፍሉ 70 ተማሪዎች በአንድ አፍ በአንድ ላይ "ጥቁር ነጥብ" የሚል መልስ ሰጡ፡፡ አስተማሪው ግን በሰጡት መልስ ገሰፃቸው፡፡

"አሁን እናንተ ናችሁ ተምራችሁ ይህችን ሃገር የምትለውጡት?! ነጩን፣ ሰፊውን፣ ትልቁን ሰሌዳ ሳታስተውሉ እንዴት ትንሿ ጥቁር ነጥብ ታየቻችሁ!? ሰፋ አድርጋችሁ አስቡ፣ ሰፋ አድርጋችሁ እዩ እንጂ!!" አላቸው፡፡ ኮፊ አናን "ይህቺ አጋጣሚ እና የመምህሩ አባባል ከአካባቢዬ አርቄ ስለሃገሬ፣ ስለዓለም ሰፋ አድርጌ እንዳስብ እንድመለከት ተፅዕኖ ያሳደረብኝ ይመስለኛል" የሚል ምላሽ ነበር ለጋዜጠኛዋ የሰጧት፡፡

ልክ እንደዚያው ሁሉ፤ አሰፋ ጫቦ በመጣጥፎቹ ነገሮችን ሠፋ አድርገን እንድንመረምር፣ አርቀን እንድንመለከት ነው በተለያዩ ጊዜ፣ የተለያዩ አጋጣሚዎችን በማውሳት የሚወተውት ፀሐፊ ነው፡፡ በ1993 ዓም የ"ኢትኦጵ" ጋዜጣና መፅሔት ም/አዘጋጅ ሆኜ በምሰራበት ጊዜ "ለኢትዮጵያ አንድነት ደርግ ሺ ጊዜ ይሻላል" የሚል ፅሁፍ እንድናትመለት ለዝግጅት ክፍላችን ልኮ ነበር፡፡ ከዋናው ፅሁፍ ጋር ለአዘጋጁ ማሳሰቢያ ጭምር አያይዞ ነበር የላከው፡፡ "…የኢሠፓ ጉዳይ በሰብዓዊነት ደረጃም፣ በእምነት ደረጃም፣ በፖለቲካም፣ በሕግም…በፈለገው ነጥብ፣ አንድ ቀን አንድ ነጥብ ላይ መዘጋት ይኖርበታል፡፡…" ይላል ማሳሰቢያው፡፡

አሠፋ ፅሁፉ ደቃቃ፣ የፊደል አጣጣሉ ልቅም ያለ መሆኑን በደንብ ያየሁት ያኔ ነው፡፡ የፅሁፉ ፈትለ-ነገር (Team) በዚያ ወቅት በኢሠመጉ አመራር አባላት መሀከል የሃሳብ ውዝግብ መከሰቱ ነበር፡፡ የኢሠፓ አባላት የነበሩ ሰዎች የኢሠመጉ አባል መሆን የለባቸው የለባቸውም የሚል ነበር የውዝግቡ መንስኤ፡፡

አሠፋ ጫቦ ለኢሰመጉ መመስረት መሰረት የጣለው እሱ መሆኑን፣ ፕ/ር መስፍን ወልደማሪያም ጅምር ሃሳቡን አጠናክረው ቀጥለውበት ኢሰመጉን እንደተቋም የገነቡና ያስቀጠሉ መሆናቸውን ያወደሰበት ፅሁፍ ነበር፡፡ እናም ወደ ዋናው ጉዳይ ዘልቆ እንዲህ ይላል፡-

"..ኢሠፓ የፖለቲካ ድርጅት ነበር። ...ፖለቲካ ደግሞ ማህበራዊ ሣይንስ (Social scince) ነው። ማህበራዊም ፖለቲካዊም ጥበብ (art) ነው ይላሉ። (poletics is the art of Compromise)ም ነው ይሉታል።ፖለቲካ የመቻቻል ጥበብ ነው ለማለት የፈለጉ ይመስለኛል።... "

አሠፋ ጫቦ በርካታ ተመክሮዎችን ያወሳል። ከአፍሪካም ከአለም ዙሪያም ክስተቶች ያጣቅሳል። እኔን የመሰጠኝ የዚህ መካር ፅሁፉ ማሳረጊያ ነው።

"...ማለት የፈለግኩት፣ ኢሰፓም ሆነ ደርግ ላይ እቋም ሲወሰድ፣ ይህ ጉዳይ ‹የጋራ ቤታችን› ላይ ሊያሳድር የሚያሳድረውን ተፅዕኖ ግራ ቀኙን ማየት ጥሩ ነው ለማለት ነው። ትናንትና አልፎ ዛሬ ሲመጣ የጊዜ መግፋት ራሱ የሚያመጣውን ለውጥ ግምት ውስጥ እናስገባ ለማለት ነው። ‹የጠላቶቻችን ጠላት›፣ ‹ጠላት›፤ ‹የጠላቶቻችን ጠላት› ‹ወዳጃችን› አለመሆኑን ለመጠቆም ብቻ ነው። ፓኮውን ከፍተን እንይ ለማለት ብቻ ነው። ‹የጠላት› ያሉት የወዳጅ መንደር ሊሆን ይችላል። የቅራኔ አያያዝ ደረጃ ነው። በፖለቲካ ቋሚ ወዳጅ እንደሌለ ሁሉ ቋሚ ወዳጅም ላይኖር ይችላል። የሚያገናኘን አንድ መድረክ አለ። ‹የጋራ ቤታችን› በሆነ ባልሆነው እንዳይደከም ነው። ይኸው ነው።ጨረስኩ!!... "

እኔም የትውስታ ፅሁፌን መጨረስ ያለብኝ ይመስለኛል።

## <u>የመጨረሻው መጨረሻ</u>

አቶ አሠፋ ጫኮ የረቀቀ እና የላቀ የሥነ ፅሁፍ ችሎታ ያለው ሰው ነው።ችሎታው በበርካታ ዘመናት (50 ዓመታት) የዳበረ የተገነባና የገዘፈ ነው። የ13 እና የ14 ዓመት ልጅ እያለ ነው መፃፍ የጀመረው። የ7ኛና የ8ኛ ተማሪ ሳለ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የፃፈው ፅሁፍ በመምህሩ "ጋሽ አበበ" highly appreciate የሚል ሙገሳ የተቸረው ነው።

በ1950ዎቹ አጋማሽ ፅሁፉን ወደ ጋዜጣ ይልክ ነበረ። በዚያው ዘመን ግድም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የ"ጥበብ አምድ" ነበረው። በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንም ሳምንታዊ ፕሮራም ያቀርብ ነበር። ይህንን ልምዱን የእኛን ትውልድ ፀሐፊያን ለማበረታት "ደፍሮ መፈተሽ ነው" በሚል ርዕስ (በኢትኦጵ ጋዜጣ የየካቲት ወር 7 እና 15 ቀን 1993) አስፍሮታል።

" ... የምፅፈውን እንድፅፍ ማን፣ ምን እንደገፋኝ እርግጠኛ አይደለሁም። ፃፍ ፃፍ የሚል ኡቃቤ አምላክ ሳይኖር አይቀርም።...እንዳቅሚቲ ፃፍ ፃፍ የሚል ማዕድን ውስጤ አለ ማለት ነው። ማእድኑ ሁላችንም ውስጥ አለ። የሌለው ሰው የለም ማለት ነው።...ቀለም የቆጠረ ሁሉ ፀሐፊ መሆን ይችላል። ያልቆጠረም ፀሐፊ ነው። አሳምሮ ታሪክ ነጋሪ፣ አሳምሮ ተረት ነጋሪ ፀሐፊ ነው።... እያንዳንዳችን ውስጥ የተደበቀ ፀሐፊነት አለ። ዋናው ነገር ፈትሾ፣ በርብሮ

የማውጣት ጉዳይ ነው፡፡ አንዴ ከወጣ፣ ሰው ካየው ተመልሶ ግባ ቢሉትም አይገባም፡፡… አንድ የማውቀውን እውነት ቢያንስ ለአንድ ሰው ባስተላልፍ የሚል እምነት አለኝ፡፡ እኔ የምፅፈውን አይቶ፣ እኔ የምፅፈውን ሰምቶ "እኔም እችላለሁ" የሚል አንድ ሰው ብቅ ቢል ደስ ይለኛል፡፡.. "

አሠፋ ጫቦ ይህ ምኞቱ በእጥፍ የሰመረለት ሰው ነው፡፡ አንድ አይደለም ብዙ ፀሐፊዎችን አፍርቷል፡፡ አሻራውን በብዙዎች ውስጥ አትሟል፡፡ ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ (ደራሲ) ይህንን እውነት በአካል አግኝቶ መስክሮለታል፡፡ ደራሲ እንዳለጌታ ከበደ ባለፈው ሳምንት እማኝነቱን ሰጥቷል፡፡ እኔም ከዚህ ፅሁፍ አስቀድሜ "የቃሊቲ ምስጢሮች" በተሰኘው መፅሐፌ መግቢያ የተፅኖውን ኃያልነት ተናግሬአለሁ፡፡ ሌሎችም እጅግ ብዙ ወጣቶች ፈለጉን መከተላቸውን አውቃለሁ፡፡ እንዲህ በይፋ የመግለፅ እድል አላገኙም እንጂ!!

የሆኖ ሆኖ ይህ ብዙዎችን የማረከ ፀሐፊ፣ ይህ የበርካታ ዘመናት ልምድን ያካበተ፣ የበርካታ እውቀት ባለቤት፣ እንደዘበት ከሃገሩ ወጥቶ፣ በዚያው ጭልጥ ጥፍት ማለቱ ነው የሚያሳዝነው፡፡ በየጊዜው የፃፈልንን፣ በፃፈልን መጣጥፎች ውስጥ ወደፊት ሊፅፈልን ቃል የገባልንን ታሪኮች ጠርዞ፣ ደጉሶ፣ ለእኛ እና ለተተኪው ትውልድ፣ በእሱው አገላለፅ "ለጋራ ቤታችን" በሃብትነት ያበክትን ዘንድ መጠየቅ ነው፡- የዚህ ፅሁፍ ዓላማ፡፡ በጥቅሉ፤ እንደው በጥቅሉ የደራሲ እንዳለጌታ ከበደን "የት ነው ያለኸው?!" የሚል የጥሪ ድምፅ ማስተጋባትን ያለመ ነው፡፡ "አንተ እንደምን አለህ? እኛ እንዳለን አለን" የሚል የእክብሮትና የውዴታ ሰላምታ ለማቅረብ ጭምር ነው፡፡ በብዙዎች ወጣት ፀሐፊያን ልቦና ውስጥ ሰፍተህ ተንሰራፍተህ ያለህ የእኛ "ወጋጎዳ" ነህ ለማለት ነው፡፡ አበቃሁ!!